IB DIPLOMA PROGRAMME
PROGRAMME DU DIPLÔME DU BI
PROGRAMA DEL DIPLOMA DEL BI

**AMHARIC A1 – HIGHER LEVEL – PAPER 2**
**AMHARIQUE A1 – NIVEAU SUPÉRIEUR – ÉPREUVE 2**
**AMHARE A1 – NIVEL SUPERIOR – PRUEBA 2**

Tuesday 11 May 2004 (morning)
Mardi 11 mai 2004 (matin)
Martes 11 de mayo de 2004 (mañana)

2 hours / 2 heures / 2 horas

INSTRUCTIONS TO CANDIDATES

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Answer one essay question only. You must base your answer on at least two of the Part 3 works you have studied. You may include in your answer a discussion of a Part 2 work of the same genre if relevant. Answers which are not based on a discussion of at least two Part 3 works, will not score high marks.

INSTRUCTIONS DESTINÉES AUX CANDIDATS

- N'ouvrez pas cette épreuve avant d'y être autorisé(e).
- Traitez un seul sujet de composition. Vous devez baser votre réponse sur au moins deux des œuvres de la 3e partie que vous avez étudiées. Le cas échéant, vous pouvez inclure dans votre réponse une discussion sur une œuvre du même genre littéraire étudiée dans la 2e partie du programme. Les réponses qui ne sont pas basées sur au moins deux des œuvres de la 3e partie n'obtiendront pas une note élevée.

INSTRUCCIONES PARA LOS ALUMNOS

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Elija un tema de redacción. Su respuesta deberá basarse en al menos dos de las obras estudiadas en la Parte 3. Se podrán hacer comentarios sobre una obra de la Parte 2 del mismo género, si fuera necesario. Las respuestas que no incluyan una discusión sobre al menos dos obras de la Parte 3 no recibirán notas altas.

*ከሚከተሉት በአንዱ ላይ ሀተታ ፃፍ(ፃፊ):: መልስህ በክፍል 3 ባጠናሀቸው (ባጠናሻቸው) ቢያንስ ሁለት ስራዎች ላይ መመስረት አለበት:: በክፍል ሁለት ስር ከሚገኝ አንድ ተመሳሳይ የስነጽሁፍ ዘርፍ ማጣቀሻ ማስገባት ይፈቀዳል:: በክፍል 3 ባጠናሀቸው (ባጠናሻቸው) ቢያንስ ሁለት ስራዎች ላይ ያልተመሰረተ መልስ ከፍተኛ ነጥብ አያስገኝም::*

**ድራማ**

1. ተከታዩን

(ሀ) ትራጀዲና ኮመዲ የተለያዩ ቢሆኑም ሁለቱም የህይወትን ጠቃሚ ገጽታ በማሳየታቸው ይመሳሰላሉ:: ያጠናሃቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በመጥቀስ ይህንን ሃሳብ አስረዳ::

ወይም ቀጣዩን ምረጥ::

(ለ) ድራማ ስነጽሁፋዊ የጥበብ ዘርፍ እንዲሁም ለእይታ የሚቀርብ ጥበብ ነው:: እንደ ሌላው የስነጽሁፍ ዘርፍ ሁሉ ረቀቅ ያለ በመሆኑ አንድ ጊዜ ለእይታ ሲቀርብ በጽሁፉ ውስጥ የሚገኘው ሃሳብና የጽሁፉ መንፈስ ሁሉ አይንፀባረቅም:: ይህንን ሃሳብ ያጠናሃቸውን ሁለት ድራማዎች በመመርኮዝ ግለጽ::

**ረጅም ልቦለድ**

2. ተከታዩን

(ሀ) የልቦለድ መቼት ጠቀሚ ነው የሚባለው ስለገፀባህሪያቱና ስለሚገጥሙዋቸው ውጣውረዶች ያለን አመለከከት ላይ ተጽእኖ በማሳደር ለትረከው የሚኖረንን አስተያየት በመወሰኑ ነው:: ያነበብካቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በማነፃፀር ይህንን ሃሳብ ግለጽ::

ወይም ቀጣዩን ምረጥ::

(ለ) አንድን የልቦለድ ገፀባህሪ በፍጥነት ለመረዳት ገፀባህሪው የሚናገረውን ሁሉ በጥንቃቄ መመልከት ይገባል:: የንግግሩን ይዘት ብቻ ሳይሆን የአጻጻፍ ስልቱንም መመርመር ያስፈልጋል::ይህ አይነቱ ጥናት አንድን ገፀባህሪ ለመረዳት ምን ያህል ያግዛል? ያነበብካቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በማነፃፀር ሃሳብህን አስረዳ::

**ስነግጥም**

3. ተከታዩን

(ሀ) የአንድ ግጥም ውበት ግጥሙ ባለው ሙዚቃዊ ለዛ ማለትም በረቂቅ ዜማዊ አቀራረቡ ይወሰናል:: በዚህ ሃሳብ ምን ያህል ትስማማለህ?

ወይም ቀጣዩን ምረጥ::

(ለ) ጥሩ የግጥም አንባቢ ለምፀት እንዲሁም በግጥም ውስጥ ላሉ ንጽጽራዊ ዘይቤዎች ልዩ ትኩረት ሊሰጥ ይገባዋል የሚለውን ሀሳብ ያነበብካቸውን ግጥሞች በመጥቀስ አብራራ::

**ስድንባብ**

4. ተከታዩን

(ሀ) የአንድ ስድ ጽሁፍ(ለምሳሌም ወግ) ዋና አላማ አንባቢውን ማሳመን መቻሉ ነው። ይህንን ሃሳብ አብራራ።

ወይም ቀጣዩን ምረጥ።

(ለ) አንድን ስድ ጽሁፍ (ለምሳሌም ወግ) የተዋጣለት የሚያደርገው የጽሁፉ ይዘት ብቻ ሳይሆን ጽሁፉ የቀረበበት መንገድም ጭምር ነው። ይህንን ሃሳብ ግለጽ።

**አጭር ልቦለድ**

5. ተከታዩን

(ሀ) የአጭር ልቦለድ ጭብጥ አንባቢው የተለያዩ ትንታኔዎች በማድረግ የሚያገኘው እንጂ በግልጽ ተቀምጦ የሚገኝ አይደለም። የአጭር ልቦለድን ጭብጥ ለማግኘት የሚረዱ መንገዶች የትኞቹ ናቸው?

ወይም ቀጣዩን ምረጥ።

(ለ) የአንድ አጭር ልቦለድ ገፀባህሪያት ግለወጥ (እንዲሁ የማይለዋወጡ) መሆን አለባቸው። ይህንን ሃሳብ ያጠናሃቸውን ሁለት ስራዎች በምሳሌነት በማወዳደር አስረዳ።

**6. ሁለገብ (አጠቃላይ)**

ከሚከተሉት አንዱን መርጠህ መልስ(ሽ)።

(ሀ) የአንድ የስነጽሁፍ ስራ የትረካ አቅጣጫና ታሪኩ የተነገረበት ሁኔታ ለልቦለዱ የሚኖረን ግንዛቤ ላይ ተጽእኖ ያሳድራል በሚለው ሃሳብ ትስማማለህ? ለምን?

ወይም

(ለ) ስነጽሁፋዊ ስልት አንድ ደራሲ ሀሳቡን የሚያቀርብበት የራሱ የሆነ መንገድ ነው። ይህንን ሃሳብ ያጠናሃቸውን ሁለት ስራዎች በምሳሌነት በማወዳደር አብራራ።

ወይም

(ሐ) ስነጽሁፍ የሚያቀርበው እውነታን ቢሆንም በስነጽሁፍ የሚቀርበው ጉዳይ በገሀዱ አለም የተከሰተ አይደለም። ያጠናሃቸውን ሁለት ስራዎች በምሳሌነት በመጥቀስ ሀሳብህን ግለጽ።

ወይም

(መ) ስነጽሁፍ ህይወትን እንድንገነዘብ የሚያደርገን ሲሆን ህይወትም እንዲሁ ስነጽሁፍን እንድንረዳ ያግዘናል። ይህንን ሃሳብ በምሳሌ አስረዳ።

---